# የትምህርት ቁርስ እና ምሳ

እንዴት የተማሪዎች አካውንት እንደሚሰራ

ሁሉም ተማሪዎች በሾርላይን ትምህርት ዲስትሪክት ስር ሲመዘቡ የራሳቸው የሆነ የተማሪ መታወቂያ ቁጥር እና የምግብ አካውንት ይሰጣቸዋል። ይህ አካውንት ከቼክ አካውንት ጋር ይመስላል። በተጠቀሙ ጊዜ በውስጡ የተቀመጠው ብር መጠንም በአንጻሩ ይቀንሳል። በትምህርት አመቱ መጀመሪያ ላይ ለእያንዳንዱ ተማሪዎች ባር ኮድ ካርድ ይሰጣቸዋል። ተማሪዎች ምግብ ለመግዛት ይህንን ካርድ መጠቀም ይችላሉ። ተማሪዎች ምግብ ከመግዛታቸው በፊት አስተማሪዎች የካርዱን አጠቃቀም ያስተምሮቸዋል። የመካከለኛ እና የከፍተኛ ደረጃ ተማሪዎች የመታወቂያ ቁጥራቸውን በማስገባትመጠቀም ይችላሉ።

**ክፍያ**

በብዙ አይነት መንገድ ወደ ልጅዎት አካውንት ገንዘብ ማስገባት ይችላሉ፤

- *ተመራጭ መንገድ * በዴቢት ወይንም ክሪዲት ካርድ በኦን ላይን መክፈል፦ https://touchbase.shorelineschools.org/
- ጥሬ ገንዘብ ለካፍቴርያው ካሽር መክፈል።
- ድንገተኛ ካስፈለገ በስልክ ዴቢት ወይንም ክሬዲት ካርድ በስልክ ቁጥር 206-393-4102 መክፈል ይቻላል።
- Hamlin Park at 2003 NE 160th ጀርባ ያለው የፉድ ሰርቪስ ቢሮ በማንኛውም የክፍያ መንገድ መክፈል ይችላሉ።

በአመቱ መጨረሻ የቀረው ቀሪ ገንዘብ ተማሪው በሾርላይን ትምህርት ዲስትሪክት እስከቀጠለ ድረስ ገንዘቡ ለሚመጣው አመት ይሻገራል።

የአካውንቱ እንቅስቃሴ፤

ኦን ላይን ላይ በመሄድ የፋሚሊ አክሰስ ፔጅ ላይ (Food service)የሚለውን በመጫን የአካውንቱን እንቅስቃሴእና የተገዛውን ማየት ይችላሉ። በኦን ላይን ከከፈሉ ደግሞ በዛው ገፅ ላይ የFood service አገልግሎት ማግኘት ይችላል። የ*Family access (ፋሚሊ አክሰስ)* መግቢያ ከሌሎት ት/ቤት ቢሮ ያነጋግሩ። የምግብ አገልግሎት ወብ ሳይት ይህ ወብ ሳይት ላይ ብዙ የተለያዩ መረጃ ያገኛሉ፤

- የምግብ አይነት ማውጫ መረጃ።
- የነፃ ወይም የቅናሽ ምግብ ኣመልከቻ፣ መመሪያ እና በተደጋጋሚ የሚነሱ ጥያቄዎችን።
- ዋጋ እና ክፍያ መረጃ።
- ወደ USDA ህግ መግቢያ ገፅ ያመለክታል።
- የአውቶሜት (automated "Negative Balance Notifications") የገንዘብ መቀነሱን ወይንም ካስቀመጡት ገንዘብ በላይ መጠቀሞን የሚያሳስብ መረጃ ለማግኘት እንዲችሉ መመዝገቢያ። የምግብ አገልግሎት አድራሻ በትምህርት ቀናት ቢሮው 7:30am to 3:30pm ይከተላል፤ ትምህርት በሌለበት ቀን ውስጥ የስራ ሰአቶች ይለያያሉ። ለማንኛውም መረጃ 206-393-4209 ይደውሉ ወይንም nutrition.services@shorelineschools.org ይጎብኙን።